Global Pulse Confederation

# *GPC Pulses የውል ቁ1*

**(ከሐምሌ 13/2017 ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆን)**

## የሙሉ ኮንቴነር ጭነት ውል (FCLs)
## በጥቅል ወይም በጆንያ
## CIF / C & F ሁኔታዎች

**ጠቃሚ ማስታወሻ፡** GPC ለመረጃና ለስልጠና አገልግሎት ዓላማ ብቻ በማሰብ የ ጂፒሲ አለማቀፍ የቅባት እህሎች ጥምረት ውል ቁጥር 1 የአማርኛ ትርጉምን አቅርቧል። ጂፒሲ የቅባት እህሎች ውል ቁጥር 1 የእንግሊዝኛ ቅጂ የበላይነት የሚኖረው ሲሆን በትርጉም ላይም ያልታሰበ ስህተተ ቢፈጠር ኦፊሴላዊው የእንግሊዝኛ ትርጉም የበላይነት አለው፡፡ በ GAFTA (ጋፍታ) የሚካሄድ ማንኛውም የግልግል ዳኝነት የሚካሄደውም በእንግሊዝኛ ነው

**እንዳግባብነቱ ይሰርዙ/ይገለጹ* *ቀን*..........................................

**ሻጮች** ..................................................................................................

**አገናኝ ደላሎች**..................................................................................................

**ገዥዎች**..................................................................................................
በሚከተሉት ደንቦችና ሁኔታዎች መሰረት በዛሬው ዕለት ይህን ውል ተዋውለዋል፡፡

**1.** የ ..................................................................................................ሥሪት የሆኑ ምርቶች

ዝርዝር መግለጫ ..................................................................................................

አስተሻሸግ በሻጭ ምርጫ * በጥቅል ወይም ጆንያ ........................................................................ይሆናል፤

**2. ብዛታቸው** ........ሙሉ የሆኑ ኮንቴነሮች እያንዳንዳቸው በግምት የሚያዙት........... ሜትሪክ ቶን ተብሎ ተገምቷል። በሻጭ ምርጫ ቢበዛ ወይም ቢያንስ እስከ 5% ያለ ልዩነት በውሉ ይስተናገዳል፡፡ በዚህ መልክ ማስተናገድ የሚቻለው በአጠቃላይ ከተጫኑት እቃዎች አንፃር እየታየ ነው፤ በእያንዳንዱ ኮንቴይነር ላይ ግን መቻቻል አይኖርም፡፡

**3. ዋጋ እና መዳረሻ**
* የ1000 ኪሎ ግራም ወይም አንድ ቶን የዋስትና የወጪና የማጓጓዣ ዋጋ ወደ .......................................................... በሆነ ዋጋ
* የ1000 ኪሎ ግራም ወይም አንድ ቶን የወጪና የማጓጓዣ ዋጋ ወደ ..........................................................

**4. የድለላ ክፍያ**
የድለላ ክፍያ የሚፈጸመው በሻጮች ሲሆን በው ላይ በተመለከተው አማካይ ጭነት መሰረት በእያንዳንዱ ቶን ላይ ነው፡፡ በጭነት ክልከላ ውል ላይ ከሚደረግ የውሉ መሰረዝ በስተቀር እቃው ቢጠፋም ባይጠፋም እንደውሉ ቢሟላም ሆነ ሳይሟላ ቢቀር ክፍያው ይፈጸማል፡፡ የድለላ ክፍያ የሚከፈለው የጭነት ሰነዶች ልውውጥ በተደረገበት ቀን፣ ወይም ዕቃዎቹ ካልተወሰዱ፣ ዕቃዎቹ ከተወሰዱበት ቀን ቀጥሎ ባለው ጀምሮ ከሚቆጠር ተከታታይ 30ኛ ቀን ላይ ነው፡፡

**5. ጥራት**
በተቃራኒው ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር፣ የተላከውን ጭነት በተመለከተ ከመንግስት፣ ከባለስልጣን ወይም በ Gafta አውቅና ካለው ገለልተኛ መርማሪ አካል የተሰጠ ማስረጃ የመጨረሻ ተደርጎ ይቆጠራል።
ሻጮች በገለልተኛ አካል የተዘጋጀ የምስክር ወረቀት (ለምሳሌ፡ በገለልተኛ አካል ባልተዘጋጁ ናሙናዎች ላይ የተመሰረቱ ወይም የተላኩትን ዕቃዎች ከተመረመሩት ዕቃዎቸ ለመለየት የማያስችሉ) ለማቅረብ ካልቻሉ፣ ገዥዎች ኮንቴነሩ በተከፈተ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ናሙናዎቹን ወስደው እንዲያሽጉ ለተወካዮቻቸው መመሪያ የመስጠት አማራጭ ያላቸው ሲሆን ይህም የሚደረገው ዳግም ደረጃ ለመስጠት እና/ወይም ትንተና ለማካሄድ ነው። የሻጮች ተወካዮችም ገዥዎ ናሙና ለመውሰድ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንደደረሳቸው ናሙናው በሚወሰድበት ቀን በቦታው ላይ መገኘት ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ ገዥዎችና ሻጮች የዳግም ደረጃ አሰጣጥ/ትንተና ውጤትን ለመቀበል ይስማማሉ። ናሙና ለመውሰድ፣ ዳግም ደረጃ ለመስጠት እና/ወይም ለትንተና ስራ የሚወጣው ወጪ ግማሹ በገዥዎችና ቀሪው ግማሽ ደግሞ በሻጮች ይከፈላል።
ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ በ .................................................... የተደረገ ማጠን (በሚመለከታቸው ወገኖች ስምምነት ከተደረገበት ብቻ)
**ሁኔታ፤** ጭነቱ መላክ ያለበት በጥሩ ሁኔታ ነው።

**6. የጭነት ጊዜ ስለማራዘም**
ለጭነት በውል የተፈቀደው ጊዜ ገደብ ከ8 ቀናት ለማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊራዘም የሚችል ሲሆን ይህ የሚሆነው ቢዘገይ ሻጮች በመጀመሪያ የተቀመጠው ቀን ካለፈ በኋላ ቀጥሎ ካለው የሥራ ቀን የማያልፍ የጊዜ ማራዘሚያ ማስታወቂያ ሲሰጡ ነው፡፡ ማስታወቂያው የተጠየቁ ተጨማሪ ቀናትን የግድ መጥቀስ አያስፈልገውም።

ሻጮች ለገዥዎች የተወሰነ ልዩ ወጪ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን ይህም ገንዘብ መጀመሪያ የተገለጸው የጊዜ ገደብ በታለፈባቸው ቀናት ብዛት ላይ ተመስርቶ ከውል ዋጋ ላይ በኢንቮይሱ ውስጥ ይቀነሳል፤ ተግባራዊ የሚሆነው መለኪያም የሚከተለው ነው፡-

ከ1 እስከ 4 ተጨማሪ ቀናት፣ 0.50%፤

ከ 5 እስከ 8 ተጨማሪ ቀናት፣ 1%፤

ይሁን እንጂ፣ ከላይ በተገለጸው መሰረት ለገዥዎች ማስታወቂያ ከደረሳቸው በኋላ ሻጮች በእነዚህ 8 ቀናት ውስጥ ለማስረከብ ካልቻሉ፣ ውሉ መጀመሪያ በተገለጸው ጊዜና ተጨማሪ 8 ቀናት ውስጥ ከውል ዋጋው ላይ 1% ተቀንሶ የሚጸና ሲሆን ማንኛውም የጉዳት ካሳ የሚሰላውም በዚሁ መሰረት ይሆናል። በዚህ አንቀጽ መሰረት ልዩ ወጪ መከፈል ካለበት፣ የውል ዋጋ የሚሆነው የመጀመሪያው የውል ዋጋ ሲቀነስ ልዩ ወጪ ሲሆን ሌላ ማንኛውም የውል ነክ ልዩነት በዚህ የተቀነሰ ዋጋ ላይ ተመስርቶ መከፈል አለበት።

## 7. ጭነት የሚላክበት ጊዜ

በጭነት ሰነድ (ወይም በኢንተርሞዳል የትራንስፖርት ሰነዶች) መሰረት ቀን የተጻፈበት ወይም የሚጻፍበት ........................................................................

(ሀ) የጭነት ሰነድ/ዶች (ወይም የኢንተርሞዳል የትራንስፖርት ሰነዶች) ቀን የሚጻፍባቸው ዕቃዎቹ በመጀመሪያው የሚጠበቅ መርከብ ላይ በእርግጥ የተጫኑ ሲሆን ወይም

(ለ) የጭነት ሰነድ/ዶች (ወይም የኢንተርሞዳል የትራንስፖርት ሰነዶች) ዕቃዎቹ ለኮንቴነር አቅራቢው ሲደርሱ ቀን የሚፃፍባቸው፡፡

ምናልባት እነዚህ ወገኖች ከላይ በቀረቡት አማራጮች የማይስማሙ ከሆነ፣ የጭነት ሰነዱ/ዶች ቀን የሚጻፈበት ዕቃዎቹ በተጨባጭ **"መርከብ ላይ ሲጫኑ"** ነው። በጭነት ሰነዱ ላይ ያለው ቀን ተቃራኒ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ የጭነት ቀን ማረጋገጫ ተደረጎ ይወሰዳል። በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ላይ የሚጻፉ ሌሎች ቀናት ቢኖሩ "መርከብ ላይ የተጫነበት" ቀንን ዋጋ የሚያሰጡ አይደሉም። ጎደሎ ቁጥር ያላቸው ቀናት ባሉት ማንኛውም ወር ውስጥ፣ መካከል ላይ ያለው ቀን በሁለቱም የወሩ ክፍሎች ውስጥ እንዳለ ይቆጠራል።

**8. በ C&F ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የተላከ ጭነት ማሳወቂያ** - ሻጮች የኮንቴነሩን መለያ ቁጥሮችና የሚታወቅ ከሆነም ጭነቱን እንዲያጓጉዝ የታሰበው መርከብ(ቦች) ለገዥዎች ማሳወቅ ያለባቸው ሲሆን ይህም ገዥዎች ዕቃዎቹን ኢንሹራንስ እንዲያስገቡ ያስችለዋል። ሻጮችም ዕቃዎቹ ለገዥዎች እስከሚረከቡ ድረስ ኢንሹራንስ መግባት አለባቸው። የጭነት ማሳወቂያ ከተሚላ የጭነት ርክክብ ተፈጻሚል፡፡

## 9. በስም በሚታወቁ መርከቦች የሚደረጉ ሽያጮች

በስም በሚታወቁ መርከቦች በሚያካሂዱት ሽያጭ ላይ የሚከተሉት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

(ሀ) መርከቡ የሚገኝበት ቦታ በገዥዎችና በሻጮች መካከል ስምምነት ይደረግበታል፤

(ለ) በጭነትና በአመዳደብ አንቀጽ ውስጥ "የተመደበ" ከሚለው ቃል በፊት "አሁን" የሚል ቃል መግባት አለበት፤

(ሐ)ተሸጦ ከተጫነ በአግባቡ ማስረከብ የሚለው አንቀጽ ይሰረዛል፡፡

## 10. ጭነት፣ ኮንቴነሮችና ምደባ

በስራ ላይ በአለውና የአለም አቀፍ የእቃዎች ምደባ ውል ማህበር በአወጣው የውል አመዳደብ መሰረት አንደኛ ደረጃ በሆኑና በራሳቸው ሜካኒካዊ አሰራር በሚንቀሳቀሱና ለማጓጓዝ ስራ አመቺ በሆኑ መርከብ (መርከቦች) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ምርቱ ሳይገላበጥ ጭነቱን ለስራው በሚመጥኑ ኮንቴነሮች ከ...................................................................... ለመጫን፡፡ የአገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት መከናወን ያለበት በአገር ውስጥ መርከብ ወይም ዕቃዎችን ለመቀበልና ለማጓጓዝ ተስማሚ በሆነ ጀልባዎች ነው።

## 11. ርክክብ

(ሀ) የርክክብ ማስታውቂያ መጀመሪያ የሚጭነውን መርከብ ስም፣ የተጓጓዘውን ጭነት ግምታዊ ክብደት፣ እና የጭነት ሰነድ ቀን ወይንም ግምታዊ ቀን እና የኮንቴነሩን ቁጥርን መግለጽ አለበት።

(ለ) የርክክብ ማስታወቂያው ከጭነት ሰነድ ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ5 የስራ ቀናት ውስጥ አስጫኙ በቀጥታ ለገዥዎቹ ወይም ለሻጭ ወኪል ወይም በውል ውስጥ ለተገለጹት አገናኝ ደላሎች መድረስ አለበት።

(ሐ) የርክክብ ማስታወቂያው በንኡስ አንቀጽ (ለ) ላይ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ቀጣይ ሻጮች ለገዥዎቻቸው ወይም ለሻጭ ወኪል ወይም በውል ውስጥ ለተገለጹት አገናኝ ደላሎች መድረስ አለበት፤ ነገር ግን፣ ቀጣይ ሻጮች የጭነት ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በመጨረሻው ቀን ወይም በንኡስ አንቀጽ (ለ) ውስጥ ከተገለጸው ጊዜ በኋላ ከደረሰው፣ የርክክብ ማስታወቂያው በወቅቱ ደርሷል ተብሎ የሚቆጠረው፡

(1) በተመሳሳይ የመቁጠሪያ ቀን ውስጥ፣ በየትኛውም የስራ ቀን ከ1600 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከተሰጠ፣ ወይም

(2) ከሚቀጥለው የስራ ቀን 1600 ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በ1600 ሰዓት ውስጥ ወይንም በማንኛውም የስራ ያልሆነ ቀን ላይ ከደረሰ

(መ) ለሻጭ ወኪል ወይም በውል ውስጥ ለተገለጹት አገናኝ ደላሎች የተሰጠ የርክክብ ማስታወቂያ ለገዞዎች የተሰጠ የርክክብ ማስታወቂያ ተደርጎ ይቆጠራል። የርክክብ ሰነድ የተሰጠው ሻጭ ወኪል ወይም አገናኝ ደላሎች በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት እንደ ርክክብ ሰነድ ማስታወቂያ ያገለግላሉ። አስጫኙ ወይም ቀጣይ ሻጮች የርክክብ ማስታወቂያውን ለሻጭ ወኪል ከሰጡ፣ ይኸው ሻጭ ወኪል በቀጥታ ለገዥዎች ወይም ለአገናኝ ደላሎች የርክክብ ማስታወቂያውን ሊሰጥ ይችላል።

(ሠ) በርክክብ ማስታወቂያው ውስጥ የተገለጸው የጭነት ሰነድ ቀን ለመረጃ ብቻ የሚያገለግል እንጂ አስገዳጅነት የሌለው ሲሆን፣ የርክክብ ማስታወቂያ ለመስጠት በዚህ አንቀጽ የተቀመጠውን ጊዜ ለመወሰን ደግሞ በጭነት ሰነድ ላይ የተገለጸው ተጨባጭ ቀን የሚወሰድ ይሆናል።

(ረ) ማንኛውም የርክክብ ማስታወቂያ በሚተላለፍበት ወቅት የተፈጸመ ስህተትና ስህተቱንም ማረም የሚቻል ሲሆን ላኪውም ለዚህ ስህተትና ቀደም ሲል ለተፈጸመና በቅን ልቡና ለተደገመ ስህተት ሃላፊነት አይኖርበትም፡፡

(ሰ) የርክክብ ሰነዱ ከመድረሱ በፊት መርከቡ ከደረሰና በዚህም ምክንያት ተጨማሪ ወጪ ከወጣ፣ ይህን ወጪ መሸፈን ያለባቸው ሻጮች ናቸው።

(ሸ) ገዥዎች የህጋዊ የርክክብ ማስታወቂያ ሲደርሳቸው፣ ከእነርሱ ስምምነት ውጭ የርክክብ ማስታወቂያውን ቀሪ ማድረግ አይቻልም፡፡

## 12. ክፍያ

(a) ውሉ በተደረገበት ጊዜ በተዋዋዮች መካከል በተደረሰበት ስምምነት መሰረት ዋናውን የጭነት ሰነድ በመቀበል አግባብ የሆነው የክፍያ ዘዴ (እባክዎ የሚፈለገው ተገልጾ የማይፈለገውን ይሰርዙ)

(i) የሰነድ ማስረጃው ለአቅራቢው ባንክ በቀረበ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ የሚከፈል

(ii) የማይሻር ሌተር ኦፈ ክሬዲት እንደቀረበ የሚከፈል

(iii)....% የቅድመ ክፍያ፤ ከቀሪ ሂሳብ ....% የሰነድ ማስረጃ እንደቀረበ

(iv)ፋክስ የተደረገ ወይም ስካን ተደርጎ በኢሜይል የተላከ የጭነት ሰነዶች ኮፒ በደረሰ በ48 ሰዓታት ውስጥ

(v) ቢዘገይ መርከቡ የማራገፊያ ወደብ ላይ እንደደረሰ ሰነድ ሲቀርብ የሚከፈል

(vi) ሌላ ........................................................................................................ በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት መሰረት

**ግልጽ የሆነ ስምምነት ከሌለ፣ ክፍያ የሚፈጸመው (i) የሰነድ ማስረጃዎች ለባንኩ በቀረበሉት በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ነው፡፡**

(ለ) የጭነት ሰነዶች ውስጥ የሚካተቱ ማስረጃዎች: - 1. ኢንቮይስ። 2. ሙሉ የጭነት ሰነድ ወደ ሌላ ወገን ሊተላለፍ እና ሊዘዋወር በሚችል መልኩ ወይም የመርከብ ማስረከቢያ ትእዛዝ(ዞች)። በገዥዎች ከተፈለገ ደግሞ እነዚህ የማስረከቢያ ትእዛዞች ላይ የመርከብ ባለቤቶች፣ ወኪሎቻቸው ወይም እውቅና ያለው ባንክ መፈረም ይኖርበታል። 3. ለ CIF/CIFFO ሁኔታዎች ፖሊሲ(ዎች) እና /ወይም የኢንሹራንስ ማስረጃ(ዎች) እና/ወይም የኢንሹራንስ ደብዳቤ(ዎች) ውሉ በተፈረመበት የገንዘብ ዓይነት ይዘጋጃል። በገዥዎች ከፈለገ ደግሞ የኢንሹራንስ ደብዳቤ(ዎች) እውቅና ባለው ባንክ መረጋገጥ አለበት። 4. ሌሎች ሰነዶች ውሉ በሚጠይቀው መሰረት ይሆናሉ፡፡ ገዥዎች የመርከብ ጦርነት ማስቀረት ምክር ቤት አንቀጽ እና/ወይም ሌላ የሚታወቅ ይፋ የጦርነት ስጋት አንቀጽ የያዙ ሰነዶችን ለመቀበል ተስማምተዋል።

(ሐ) የጭነት ሰነዶች በገበር በተፈለጉ ጊዜ ወይንም መርከቡ የመድረሻ ቦታው በደረሰ ጊዜ ዝግጁ ያልሆኑ ከሆነ ሻጩ ሌሎች ሰነዶችን ይሰጣል ወይንም ገርው እቃዎችን ለመረከብ የሚረዳው ክፍያ መፈጸም ያለበት ሲሆን ክፍያ በገበር የሚፈጸመው ለዚህ ማካካሻ የሚሆኑ የሚያዘጋጁ ሲሆን ይህም ክፍያ በምንም ሁኔታ የጭነት ሰነዶቹ ዝግጁ በሚሆኑበት ጊዜ በውሉ ስር የሚመነጩ የገበር መብቶችን አያስቀረውም፡፡

(መ) ሻጮች የጭነት ሰነዶችን ወይም ገዥዎች ዕቃዎቹን እንዲረከቡ የሚያስችላቸው ሌሎች ሰነዶች ወይም ካሣ ለማቅረብ ካልቻሉ፣ ገዥዎች ከእነርሱ በሚያገኙት ካሳ መሰረት ዕቃዎቹን ተረክበው ሌሎች ሰነዶች ሲቀርቡ ክፍያ ይፈጽማሉ። ማንኛውም ምክንያታዊ የሆኑ ተጨማሪ ወጪዎች ማለትም የዚህ ካሳ ወጪዎች ወይም ሻጮች እነዚህን ሰነዶች ባለማቅረባቸው ምክንያት የወጡ ወጪዎች በሻጮች የሚከፈሉ ይሆናል፤ ነገር ግን፣ ይህ ክፍያ መፈጸሙ የጭነት ሰነዶች በሚቀርቡበት ወቅት ገዢዎች በውሉ መሰረት የሚያገኙትን መብቶች አያስቀረውም።

(ሠ) የቀረቡት የጭነት ሰነዶች ያልተሟላ የመጫኛ ሰነድ ያላቸው ከሆነ ወይም ሌሎች የጭነት ሰነዶች የጎደሉ ከሆነ፣ እነዚህ ሰነዶች እንደሚቀርቡ ማረጋገጫ እስከተሰጠ ድረስ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፤ በገዥዎች ጥያቄ መሰረት ይህ ማረጋገጫ እውቅና ካለው ባንክ ጋር በጋራ ሊፈረም ይችላል።

(ረ) የመሰብሰቢያ ወጪ የሚታሰበው በሻጮች ላይ ቢሆንም፣ ገዥዎች በመረጡት ባንክ ብቻ ሰነዱ እንዲቀርብ ከጠየቁ፣ ተጨማሪ ወጪዎችን መክፈል ያለባቸው ገዥዎች ናቸው።

(ሰ) በሰነዶቹ ውስጥ በግልጽ የሚታይ የአጻጻፍ ግድፈት መኖሩ ገዥዎች እነዚህን ሰነዶች እንዳይቀበሉ ወይም ክፍያን እንዲያዘገዩ መብት የማይሰጣቸው ቢሆንም፣ በዚህ ስህተት ምክንያት በገዥዎች ላይ የደረሰ ተጨማሪ ወጪ ወይም ኪሳራ ሃላፊነቱ የሻጮች ሲሆን ሻጮችም በተጠየቁ ጊዜ የፀደቀ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው።

(ሸ) በዚህ ውል መሰረት መከፈል ያለባቸው የገንዘብ መጠኖች ሳይዘገዩ መከፈል አለባቸው። በዚህ መልኩ ካልተከፈለ፣ አንደኛው ወገን አለመግባባት ስለመፈጠሩ ለሌላኛው ወገን በማሳወቅ በግልግል ደንቦች መሰረት ጉዳዩን ለግልግል ለማቅረብ ያለውን ፍላጎት ሊያሳውቅ ይችላል።

(ቀ) **ወለድ።** በየትኛውም ክፍያ ላይ ምክንያታዊ ያልሆነ መዘግየት ከተከሰተ፣ ክፍያው በሚፈጸምበት የገንዘብ ዓይነት የሚታሰብ ወለድ ይተምንበታል። በዚህ የወለድ ክፍያ ላይ የጋራ ስምምነት ካልተደረሰ፣ አለመግባባት እንደተፈጠረ ተቆጥሮ በግልግል ዳኝነት ይፈታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ወለድ የሚከፈለው በውሉ ሁኔታዎች ውስጥ ወይም በግልግል ዳኝነት ይከፈል ተብሎ ከተወሰነ ነው፡፡ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ሁለቱ ወገኖች በንኡስ አንቀጽ (ሀ) ስር የተጣለባቸውን በግልጽ የተመለከቱ ከሆነ የውል ግዴታን የሚሸሩ አይደሉም።

## 13. ቀረጥ፣ ታክስ፣ ወዘተ.

ሻጮች ዕቃዎቹን ለኤክስፖርት ከጉምሩክ ነጻ ያደርጋሉ። አሁንም ሆነ ወደፊት ዕቃዎቹ በተመረቱበት ሃገር ውስጥ ያሉ የኤክስፖርት ቀረጥ፣ ታክስ፣ ወዘተ የሻጮች ሃላፊነት ይሆናሉ። አሁንም ሆነ ወደፊት ዕቃዎቹ በሚላኩበት ሃገር ውስጥ ያሉ የሃገር ውስጥ ማስገቢያ ቀረጥ፣ ታክስ፣ ወዘተ የገዥ ሃላፊነት ይሆናሉ።

## 14. ክብደት መመዘን

*ዕቃው በተጫነበት ሰዓትና ቦታ በሻጭ ወጪ በ GAFTA በተመዘገበ የተቆጣጣሪዎች ማረጋገጫ በሻጮች ምርጫና ወጪ (በዚህ ረገድ፣ የጉድለት አንቀጽ ተፈጻሚ አይሆንም) ።የተመለከተው የክብደት መጠን የመጨረሻ ነው፡፡ የ GAFTA የክብደት ምዘና ደንብ ቁ 123 ሁኔታዎች በዚህ ውል ላይም ተፈፃሚ ናቸው፡፡

*በማራገፊያ ጊዜና ቦታ በገዥዎች ወጪ ምዘና የመጨረሻ ነው፡፡

* በገለልተኛ የሆነ የምድር ሚዛን ማረጋገጫ ወረቀት፣ ከተረጋገጠ ክብደቱ እንደአግባቡ ይቀነሳል፡፡

በተዋዋዮች መካከል ስምምነት ከሌለ፣ የመንግስት፣ ኦፊሴላዊ ወይም በ Gafta እውቅና የተሰጠው የገለልተኛ ተቆጣጣሪ ማረጋገጫ የተላከውን መጠን የመጨረሻ ሲሆን በዚም ጊዜ የጉድለት አንቀጽ 15 ደግሞ ተፈጻሚ አይሆንም።

## 15. ጉድለት

በጭነት ሰነድ ክብደት ላይ ያለ ማንኛውም ጉድለት በሻጮች የሚከፈል ሲሆን ማንኛውም እላፊ የጭነት ሰነድ ክብደት ደግሞ በውል ዋጋው መሰረት በገዥዎች ይከፈላል።

## 16. ማራገፍ

የንግድ መርከብ ድርጅት መርከቡ ኮንቴነሮችን ካስረከበ በኋላ ኮንቴነሮቹ በፍጥነት መራገፍ አለባቸው።

## 17. ኢንሹራንስ

**17.1 <u>በ CIF ሁኔታዎች ብቻ የተፈረሙ የኢንሹራንስ ውሎች፤</u>** ሻጮች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ያነሰ ጥቅም በማያስገኝ ሁኔታና በ የኢንሹራንስ

ሁኔታዎች ቁ 72 ላይ በተዘረዘረው መሰረት ኢንሹራንስ ማቅረብ አለባቸው፡-

(a) **<u>የተሸፈኑ፡-</u>** አደጋዎች

የካርጎ አንቀጾች (WA), ከአማካይ ተከፋይ፣ ከ 3% ፍራንቻይዝ ወይም የተሻሉ ሁኔታዎች ጋር - ክፍል 2 የቅጽ 72
የጦርነት አንቀጾች (ጭነት) - ክፍል 4 የቅጽ 72
አመጽ፣ አድማ እና የእርስ በእርስ ግጭትን የሚመለከቱ አንቀጾች (ጭነት) - ክፍል 5 የቅጽ 72

(b) **<u>ዋስትና ሰጪዎች</u>** - የሚገባው ኢንሹራንስ በመጀመሪያ ደረጃ ውል ጸሐፊዎች እና/ወይም ተቀማጭነታቸው ወይም የንግድ ስራ አድራሻቸው ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ከሆኑ ድርጅቶች መሆን አለበት፤ ለማንኛውም የሕግ ጉዳዮች ሲባል የእንግሊዝ ሃገር ተቀማጭነት መቀበልና ለንደን ውስጥ ለአገልግሎት ሂደት አድራሻ የሚያቀርብ መሆን የአለበት ሲሆን ነገር ግን ለመከሰሩ ሻጮቹ ሃላፊነት አይወስዱለትም፡፡

(ሐ) **<u>የኢንሹራንስ ዋጋ፡-</u>** በገዢዎች የሚከፈል ጦርነት አደጋ ክፍያን፣ የጠፋ ወይም ያልጠፋ ጭነት ጨምሮ ኢንሹራንስ የተገባለትን ዋጋ 2% የማያንስ፣

(መ) **<u>የጭነት መጠባበቂያ</u>** ፡- የማጓጓዣ ወጪው የሚከፈለው መርከቡ ሲደርስ ሲሆን ወይም ዕቃዎቹ በተጨባጭ እና በትክክል የደርሱ ከሆነና ኢንሹራንሱ የማጓጓዣ ወጪን የማይጨምር ከሆነ፣ ሻጮች በተመሳሳይ ሁኔታዎች ኢንሹራንስ የሚገቡ ሲሆን ይህም ኢንሹራንስ የሚሰራው የማጓጓዣ ወጪው ተከፋይ ሲሆን ወጪው ላይ የማጓጓዣ 2% ተደምሮ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ከላይ የተጠቀሱት አንቀጾች ውስጥ እንደተደነገገው ስጋቱ እስከሚያበቃ ድረስ ነው። በተጨማሪም፣ ልዩ ወይም አጠቃላይ የካሳ ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት ገዥዎቸ የሚኖራቸው ሁኔታ የ c.i.f. ዋጋ እና 2% ከተጫነበት ጊዜ አንስቶ ዋስትና እንደተገባላቸው የሚገልጽ ጽሁፍ በፖሊሲ ውስጥ መካተት አለበት።

(ሠ) **<u>የምስክር ወረቀቶች/ፖሊሲዎች</u>** ፡- ሻጮች ሁሉንም ፖሊሲዎች እና/ወይም የምስክር ወረቀቶች እና/ወይም የኢንሹራንስ ደብዳቤዎች በዚህ ውል መሰረት ማቅረብ (እንዳግባብነቱ ማህተም ካረፈባቸው) ከላይ በ(ሐ) ውስጥ ለተደነገገው ዋጋ ኦሪጂናል እና የጨመረ ዋጋ (ካለ) ማቅረብ አለባቸው፡፡ የኢንሹራንስ ምስክር ወረቀት ከተሰጠና፣ አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ሻጮች ይህን የምስክር ወረቀት በፖሊሲ መለዋወጥ እንደሚችሉ ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን ይህ የምስክር ወረቀት ሊለወጥ እንደሚችል በፊት ገጹ ላይ መጠቀስ አለበት። በገዥዎች ከተጠየቀ፣ የኢንሹራንስ ደብዳቤ(ዎች) እውቅና ባለው ባንክ ወይም በገዥዎች ዘንድ ተቀባይነት ባለው ሌላ ዋስትና ሰጪ ዋስትና ሊሰጠው ይገባል።

(ረ) **<u>አጠቃላይ ኪሳራ</u>** ፡- አጠቃላይ ወይም አሳማኝ የሆነ አጠቃላይ ኪሳራ ከደረሰ፣ ወይም የኢንሹራንሱ መጠን በሙሉ የሚከፈል ከሆነ፣ ከኢንቮይስ መጠን 2% በላይ የሆነ ዋስትና የተገባለት መጠን የሻጮች ሃላፊነት ሲሆን የፖሊሲው ባለይዞታ ደግሞ የኢንሹራንስ መጠኑን ሰብስቦ በዚሁ መሰረት ከሌላኛው ወገን ጋር ተነጋግሮ ጉዳዩን ያጠናቅቃል፡፡

(ሰ) **<u>ጥያቄ የሚቀርብበት የገንዘብ ዓይነት</u>**፡- ክፍያ የሚፈጸመው በውሉ በተመለከተ የገንዘብ አይነት ይሆናል፡፡

(ሸ) **<u>የጦርነትና የአድማ ስጋቶች አረቦን</u>** ፡- ከ0.50% በላይ የሆነ ማንኛውም አረቦን በገዥዎች ይከፈላል፡፡ የዚህ ኢንሹራንስ መጠን ዕቃው በተጫነበት ወቅት ወይም መርከቡ በጉዞ ላይ በሚሆንበት ወቅት ለንደን ውስጥ ተፈጻሚነት ካለው መጠን ከሁለቱ አንደኛው በጸሐፊዎቹ ከሚመረጠው መብለጥ የለበትም። እንዲህ ዓይነቱ እላፊ አረቦን ከገዥዎች የሚጠየቅ ሲሆን በተቻለ መጠን ደግሞ ከጊዜያዊ ኢንቮይስ ጋር መቅረብ አለበት፤ ነገር ግን፣ ከመርከቡ የመድረሻ ቀን ባላለፈ ወይም በዋጋ ተመኑ ላይ የውል ጸሐፊዎች ከተስማሙ በኋላ ከ7 ተከታታይ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ ካለበለዚያ ይህ የክፍያ ጥያቄ ዋጋ የሚኖረው በገላጋዮች አስተያየት የጊዜ መዘግየቱ ምክንያታዊ ነው ከተባለ ነው። ሻጮች የጦርነት ስጋት ኢንሹራንስ የማቅረብ ግዴታቸው በተግባር ላይ ባሉትና በጭነት ወቅት ለንደን ውስጥ ተፈፃሚ በሆኑ ሁኔታዎችና ደንቦች መሰረት የተገደበ ነው።

**17.2 በ ሲ እና ኤፍ ሁኔታዎች ለተፈረሙ ውሎች** ገዥዎች ከዚህ በላይ አንቀጽ 17.1 መሰረት ማንኛውም የመጫን ስራ ከመጀመሩ በፊት አግባብነት ያለው የኢንሹራንስ ሽፋን ማግኘት ያለባቸው ሲሆን፤ ጭነት ማግኘታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርቡ በሻጮች ሲጠየቁ የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው። ገዥዎች የተጠየቁትን ማስረጃ ለማቅረብ ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ካልቻሉ፣ ሻጮች በገዥ ወጪ በተመሳሳይ ሁኔታዎች ኢንሹራንስ የመግባት መብት (ግዴታ ሳይሆን) አላቸው።

**18. ጭነትን መከላከል**

"ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች" ማለት (ሀ) ዕቃዎች የተመረቱበት ሃገር ወይም በዚህ ውስጥ የተገለጸው ወደብ ወይም ወደቦች የሚገኙበት ግዛት በመንግስት የሚፈጸም የኤክስፖርት ክልከላ ወይም ሌላ የአስፈጻሚ ወይም የሕግ አውጭ አካል እርምጃ ማለት ሲሆን ይህም በከፊልም ሆነ በሌላ መልኩ ኤክስፖርትን የሚገድብ፣ ወይም (ለ) ማዕቀብ፣ ወይም (ሐ) የሽብርተኝነት ተግባራት ወይም (መ) ግጭቶች ወይም (ሠ) አድማ፣ ስራ መዝጋት ወይም የሰራተኞች ጥምረት ወይም (ረ) አመጽ ወይም ሁከት ወይም (ሰ) እሳት፣ ወይም (ሸ) በረዶ ወይም (ቀ) የፈጣሪ ቁጣ ወይም (በ) አስቀድመው ያልተገመቱና ሊቀሩ የማይችሉ የትራንስፖርት የጉዞ ማነቆዎች ወይም (ተ) "ከአቅም በላይ የሆነ ክስተት" ተብሎ የሚገለጽ ሌላ ማንኛውም ሁኔታ።

ሻጮች ወይም ገዥዎች የውል አፈፃፀማቸው በከፊልም ሆነ በሌላ መልኩ ከአቅም በላይ በሆነ ክስተት ምክንያት ከተደናቀፈ፣ ከአቅም በላይ የሆነው ክስተት እስከሚቀር ድረስ የዚህ ውል አፈጻጸም ታግዶ የሚቆይ ሲሆን የክፍያ ጥያቄ አቅራቢውም ክስተቱ ስለመፈጠሩ በ7 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ወይም የጭነት ጊዜው ከመጀመሩ ከ21 ተከታታይ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለመልስ ሰጪ ማስታወቂያ ከምክንያት ጋር መስጠት አለበት።

የጭነት ጊዜ ከሚጀምርበት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ከአቅም በላይ የሆነው ክስተት ለ21 ተከታታይ ቀናት ከቀጠለ፣ መልስ ሰጪዎች የ21 ቀናት ጊዜ ካበቃ በኋላ ከመጀመሪያው የስራ ቀን ሳይዘገይ ለክፍያ ጥያቄ አቅራቢዎች ማስታወቂያ በመስጠት ያልተፈጸመውን የውል አካል የመሰረዝ አማራጭ አላቸው።

ይህ የመሰረዝ አማራጭ ተግባራዊ ካልሆነ፣ ውሉ ለተጨማሪ 14 ተከታታይ ቀናት ጸንቶ የሚቆይ ሲሆን ከዚህ ጊዜ በኋላም ከአቅም በላይ የሆነ ክስተቱ ካላቆመ፣ የትኛውም የውሉ ያልተፈጸመ ክፍል ወዲያውኑ ይሰረዛል፡፡

ውሉ ወይም ያልተፈጸመው ክፍሉ ከመሰረዙ በፊት ከአቅም በላይ የሆነው ክስተት ካቆመ፣ ጥያቄ አቅራቢው ሳይዘገይ ወዲያውኑ ከአቅም በላይ የሆነው ሁኔታ ማቆሙን ለመልስ ሰጪው ማሳወቅ አለበት። ሻጮች ከአቅም በላይ የሆነው ሁኔታ ካቆመበት ጊዜ አንስቶ በውሉ መሰረት ለተረፈው ማንኛውም የመጫኛ ጊዜ ከአቅም በላይ የሆነው ክስተት ከመከሰቱ በፊት ለነበረው ጊዜ መብት አላቸው። በውሉ መሰረት ለጭነት የተተወው ጊዜ 14 ቀን ወይም ያነሰ ከሆነ፣ 14 ተከታታይ ቀናት ይፈቀዳል።

የማስረዳት ሸክሙ የክፍያ ጥያቄ አቅራቢው ሲሆን ተዋዋይ ወገኖችም በዚህ አንቀጽ መሰረት ለሚፈጠር መዘግየት እና/ወይም ግዴታን አለመወጣት አንዱ ለሌላኛው ሃላፊነት የለባቸውም፤ ይሁን እንጂ፣ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ መፈጠሩን ጠያቂ መዘግየቱ ወይም አለመፈጸሙ ምክንያታዊ መሆኑን የሚያሳይ አጥጋቢ ማስረጃ መልስ ሰጪ ከጠየቀ ማቅረብ አለበት።

**19. ማስታወቂያዎች**

በዚህ ውል መሰረት ሁለቱ ወገኖች ሊለዋወጧቸው የሚገቡ ሁሉም ማስታወቂያዎች በሚነበብ መልኩ እና በፍጥነት መደረግ አለባቸው። ለዚህ አንቀጽ ዓላማ፣ የፈጣን የግንኙነት ዘዴዎች የሚባሉት በሚከተለው መልኩ ይገለጻሉ፡- ቴሌክስ፣ ወይም በተጻፈበት ቀን በአካል የተላከ ደብዳቤ ወይም ቴሌፋክስ ወይም ኢሜይል ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴዎች ሲሆኑ መልእክቱ የተላከለት ሰው መልእክቱ መድረሱን ከተቃወመ፣ መልእክቱ መደረሱን የማስረዳት ሸክም የላኪው ሲሆን እርሱም አለመግባባት በሚፈጠርበት ወቅት የግልግል ዳኛውን(ዎች) ወይም በግልግል ዳኝነት ማቋቋሚያ አንቀጽ

መሰረት የተቋቋመውን የግልግል ዳኝነት ቦርድ በሚያሳምን ሁኔታ መልእክቱ ለተቀባዩ መድረሱን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት። ዳግም ሽያጭና ዳግም ግዥን በተመለከተ፣ ማንኛውም ማስታወቂያ ሻጮች ለገዥዎች ወይም ገዥ ለሻጩ ሳይዘገዩ ማድረስ አለባቸው፤ እንዲሁም በስራ ቀን ከቀኑ 10 ሰዓት በኋላ የተላከ ማስታወቂያ በቀጣዩ የስራ ቀን እንደደረሰ ይቆጠራል። ለደላሎች ወይም ወኪል የሚላክ ማስታወቂያ በዚህ ውል መሰረት እንደማስታወቂያ ይቆጠራል።

## 20. የስራ ያልሆኑ ቀናት

ቅዳሜ፣ ዕሁድና በይፋ የታወቁ እና/ወይም ሕጋዊ የሃገራት የበዓል ቀናት እና GAFTA (ጋፍታ) ለተወሰነ ዓላማ የስራ ቀናት አይደሉም ብሎ የወሰናቸው ቀናት የስራ ቀናት አይደሉም። ማንኛውንም ተግባር ለማከናወን ወይም ማንኛውንም ማስታወቂያ ለማድረስ የተቀመጠ ቀነ ገደብ የሚያበቃው ከስራ ቀናት ውጭ ከሆነ፣ ይሄው የጊዜ ገደብ እስከቀጣዩ የስራ ቀን ድረስ ይራዘማል። የጭነት ጊዜ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## 21. ግዴታን አለመወጣት

አንደኛው ወገን የውል ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረ የሚከተሉተ ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

(ሀ) ግዴታውን የተወጣው ወገን ግዴታውን ላልተወጣው ሌላኛው ወገን ማስታወቂያ ከሰጠ በኋላ ግዴታውን ባልተወጣው ወገን ውጭ የመሸጥ ወይም የመግዛት መብት ያለው ሲሆን ይኸው ሽያጭ ወይም ግዥ ዋጋውን ይወስናል።

(ለ) በዚህ ዋጋ ላይ ያልተስማማ ወገን አለ ወይም ከላይ በ (ሀ) ላይ የተገለጸው መብት ተግባራዊ ካልተደረገና የጉዳት መጠኑ ላይ የጋራ ስምምነት ከሌለ፣ የጉዳት መጠኑ የሚመዘነው በግልግል ይሆናል።

(ሐ) የሚከፈለው የጉዳት ካሳ መሰረት የሚያደርገው በውሉ ዋጋ እና አንድም በ”ሀ” ስር ከላይ ከተቀመጠው ዋጋ ወይንም የእቃዎቹ ትክክለኛ ወይም ግምታዊ ዋጋ (ውል የሚያቋርጥ ተግባር በተፈጸመበት ቀን) ከታች በ”ለ” ስር በተቀመጠው መሰረት መካከል ባለው ልዩነት ላይ ቢሆንም ይህ ብቻ መሰረት ሊሆን አይችልም፡፡

(መ) በጉዳት መጠን ውስጥ ሊካተቱ ከማይገባቸው መካከል ውል የተጣሰበት ወገን በቀጣይነት ከሚኖር ንኡስ ኮንትራት የሚያጣው ትርፍ ሲሆን የግልግል ዳኛ ወይም የይግባኝ ቦርድ ልዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መካተት አለበት ብሎ የሚያስባቸው ካልሆኑ በስተቀር ነው።

(ሠ) የደረሰ ጉዳት ካለ፣ መሰላት ያለበት ርክክብ በተፈጸመበት መጠን ሲሆን ይህን ያህል መጠን ያለው ርክክብ ካልተፈጸመ፣ በውሉ አማካይ መጠን ላይ ክፍያው ይመሰረታል። አንደኛው ወገን የሚኖረው ማንኛውም አማራጭ በአማካይ የውል መጠን መሰረት አድርጎ እንደተተገበረ ይቆጠራል።

(ረ) የውል ዘመኑ ካበቃ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ሻጮች የግዴታ አለመወጣት ጥያቄ ሊያቀርቡ የሚችሉ ሲሆን ግዴታ ያልተፈጸመበት ቀን የሚሆነው ሻጮች ለገዥዎቻቸው ምክር ከሰጡ በኋላ ባለው የመጀመሪያ የስራ ቀን ላይ ነው። ግዴታን አለመወጣትን የተመለከተ ጥያቄ ካልቀረበ፣ (በርክክብ አንቀጽ ውስጥ የተገለጹት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው) በውሉ ውስጥ ከተቀመጠው የርክክብ የመጨረሻ ቀን በኋላ በ10ኛ ተከታታይ ቀን ላይ የርክክብ ማስታወቂያ ካልተሰጠ ዳግም ሻጭ የውል ግዴታውን እንዳላከበረ የሚቆጠር ሲሆን የውል ግዴታ ያልተፈጸመበት ቀንም ከዚያ በኋላ ያለው የመጀመሪያ የስራ ቀን ይሆናል።

## 22. ሽክርክሪት

ሻጮች ተመሳሳይ ዕቃዎችን ወይም ከፊል አካላቸውን ከገዥዎቻቸው ወይም ከሌላ ማንኛውም ገዥ ድጋሚ ከገዙ፣ ዳግም ግዥ የተፈጸመባቸውን ዕቃዎች በተመለከተ ሽክርክሪት መፈጠሩ ታሳቢ የሚደረግ ሲሆን የግዴታ አለማክበር አንቀጽም ተፈጻሚነት አይኖረውም። (ለዚህ አንቀጽ አላማ ሲባል፣ ተመሳሳይ እቃዎች የሚባሉት ተመሳሳይ መግለጫ ያላቸው ከተመሳሳይ ሃገር የመጡ፣ ተመሳሳይ ጥራት ያላቸውና እንዳግባብነቱም ተመሳሳይ የትንተና ዋስትና ያላቸውና ጭነቱ በተመሳሳይ የጭነት ወቅት በተመሳሳይ የማራገፊያ ወደብ የሚራገፍ ከሆነ ነው)። የገንዘብ ዓይነት መለያየቱ ሽክርክሪቱን አያስቀረውም።

በውሉ ውሰጥ ያሉት የጭነት መከላከያ አንቀጽ ደንቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የዕቃዎቹ ርክክብ ካልተፈጸመ ወይም ዕቃዎቹ ተረካከበው ሰነዶች ካልቀረቡ፣ በአማካይ የውል መጠነ ላይ የተመሰረቱ ኢንቮይሶች ገዥዎችና ሻጮቻቸው በሚፈጽሙት ክፍያ ላይ ተመስርተው መከፈል አለባቸው፤ የሻጮች የኢንቮይስ መጠን እላፊ የሆነው ሂሳብ በእሽክርክሪቱ ውስጥ በአለው አነስተኛ የኢንቮይስ መጠን መሆን የለበትም። የመጨረሻ የርክክብ ቀን ካለፈ በኋላ በ15 ተከታታየ ቀናት ውስጥ ወይም ይህ ጊዜ ከማለቁ በፊት ሽክርክሪቱ ሊረጋገጥ ካልቻለ፣ ክፍያው መከፈል ያለበት ሽክርክሪቱ ከተረጋገጠ በኋላ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ነው።

ሽክርክሪቱ በተለያዩ የገንዘብ ዓይኖች የተገለጹ ውሎችን የሚያካትተ ከሆነ፣ ዝቅተኛው የኢንቮይስ መጠን ለመጀመሪያው በውል ጭነት የመጀመሪያ ቀን ባለ የገበያ ዋጋ መተካት አለበት፤ ኢንቮይሶችም በገዥውና በሻጩ መካከል በሽክርክሪቱ ክፍያ ውስጥ መወራረድ ያለበት ሲሆን ክፍውም በገበያ ዋጋና በአንፃራዊ ውል ዋጋ መካከል ባለው ልዩነት የውሉን የገንዘብ ዓይነት መሰረት በማድረግ ይሆናል።

ሻጮችና ገዥዎች ሽክርክሪቱን ለማረጋገጥ ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ያለባቸው ሲሆን በዚህ አንቀጽ መሰረት ደግሞ ሽክርክሪት መኖሩ ሲረጋገጥ፣ በሁሉም የሽክርክሪቱ አካላት ላይ የጸና ይሆናል። በሽክርክሪቱ መካከል ያሉትን ገዥዎችና ሻጮች በተመለከተ፣ ሻጮች ሰነዶቸን ለገዞዎች አለማቅረባቸው የውል ጥሰተ ተደርጎ መቆጠር የለበትም። የክፍያ ቀን ከመድረሱ በፊት በሽክርክሪቱ ውስጥ ያለ ማንኛውም ወገን በዚህ ውል ዕዳን መክፈል ያለመቻል አንቀጽ ውስጥ የተካተቱትን ማናቸውም ተግባራት ቢፈጽም፣ በሽክርክሪቱ ውስጥ ያሉ ወገኖች ክፍያ የሚፈጽሙት በዚሁ አንቀጽ ውስጥ በተደነገገው የመዝጊያ ክፍያ መሰረት ነው፤ ይህም በሽክርክሪቱ ውስጥ ካለ ዝቅተኛ የደረሰኝ ዋጋ ይልቅ ለክፍያ መሰረት ሆኖ ያገለግላል። በዚህ ረገድ፣ የሚመለከታቸው ገዥዎች ለሻጮቻቸው ወይም የሚመለከታቸው ሻጮች ለገዥዎቻቸው በመዝጊያ ዋጋና በውል ዋጋ መካከል ያለውን ልዩነት ይከፍላሉ።

## 23. ዕዳን መክፈል አለመቻል

ይህ ውል ከመፈረሙ በፊት አንደኛው ወገን ክፍያዎችን የሚያቋርጥ ከሆነ፣ ዕዳ ለመክፈል አለመቻሉን ወይም ዕዳ መክፈል ማቋረጡን ወይም ሊያቋርጥ መሆኑን ለአበዳሪዎቹ ካሳወቀ፣ የአበዳሪዎች ስብሰባ ከጠራ ወይም ስብሰባ ካካሄደ፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሁኔታ ካመቻቸ፣ አስተዳደራዊ ትእዛዝ እንዲሰጠ ካደረገ፣ የመፍረሰ ውሳኔ ካሰጠ፣ ተረክቦ የሚያስተዳድር ሰው ከተሾመለት፣ ወደ መፍረስ ለመግባት ስብሰባ ከጠራ ወይም ካካሄደ (ለዳግም ግንባታ ወይም ለማዋሃድ ከሚደረገ ስብሰባ በስተቀር) በ1986 በወጣው ዕዳን መክፈል አለመቻልን በሚመለከተው ሕግ አንቀጽ 252 መሰረት ጊዜያዊ ትእዛዝ ከወጣበት ወይም በእርሱ ላይ የኪሳራ አቤቱታ ከቀረበበት (እነዚህ ተግባራት ከዚህ በኋላ "ዕዳን ያለመክፈል ተግባር" ተብለው ይጠራሉ) ይህን ዕዳን ያለመክፈል ድረጊት የሚፈጽመው ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን ወዲያውኑ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን ይህ ሁኔታ ሲረጋገጥም (በውሉ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን ወይም ዕዳን መክፈል ያለመቻል ድርጊት የፈጸመው አካል ተረካቢ፣ አስተዳዳሪ፣ ንብረት አጣሪ ወይም ወኪል) ዕዳን መክፈል ያለመቻል ሁኔታ በተከሰተ በ2 የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቁን የሚያረጋግጥ ሲሆን ውሉም ማስታወቂያ ከተሰጠ በኋላ ባለው ቀጣይ የሰራ ቀን በሚኖር የገበያ ዋጋ መዘጋት አለበት።

ይህ ማስታወቂያ ካልተሰጠ፣ ሌላኛው ወገን ዕዳን ያለመክፈል ድርጊቱ መከሰቱን እንዳወቀ በዚሁ ዕለት ባለው የገበያ ዋጋ ወይም እዳን ያለመክፈል ተግባር ከተፈፀመ በኋላ ባለው ቀጣይ የስራ ቀን በሚኖር የገበያ ዋጋ የውሉን መዘጋት ወይም መሰረዝ የመግለጽ አማራጭ አለው።

በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ፣ ሌላኛው የውሉ አካል በዳግም ግዥ ወይም ዳግም ሽያጭ አማካይነት በውሉ መዝጊያ ቀን ላይ የማጠናቀቂያ ዋጋን የማረጋገጥ አማራጭ ያለው ሲሆን በውል ዋጋ እና በዳግም ግዥ ወይም ዳግም ሽያጭ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት በውሉ መሰረት የሚከፈል ወይም የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

## 24. ቋሚ አድራሻ

ይህ ውል በእንግሊዝ ሃገር ውስጥ እንደተዘጋጀና እንግሊዝ ውስጥ ተግባራዊ እንደሚሆን የሚታሰብ ሲሆን፣ ማንኛውም ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም ይህ ውል በእንግሊዝ ሃገር ህጎች መሰረት የሚተረጎምና የሚተገበር ይሆናል። በዚህ ውል የግልግል አንቀጽ መሰረት የተሰጠ ውሳኔን ለማስፈጸመ ካልሆነ በስተቀር፣ የእንግሊዝ ሃገር ፍርድ ቤቶች የማንኛውም የውሉን አካል አፈጻጸም ለመወሰን (ለክስ ወይም ለተከሳሽ ከሳሽ ዋስትና ለማግኘት ካልሆነ በስተቀር፣ ከግልግል ዳኝነት ሂደት ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶችን ስላላቸው ስልጣን እና በግልግል ዳኝነት አንቀጽ መሰረት ከግልግል ዳኞች እና የይግባኝ ቦርድ ስልጣን ውጪ የሚወድቁ ማንኛውም አይነት አለመግባባቶችን ለመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡ ለየትኛውም የፍርድ ሒደት ዓላማ ሲባል፣ እያንዳንዱ ወገን መደበኛ ነዋሪነቱ ወይም የንግድ ስራ የሚያከናውንበት ቦታ በግሬን ኤንድ ፊድ ትሬድ አሶሴሽን (GAFTA) እንደሆነ የሚቆጠር ሲሆን ተቀማጭነቱ ወይም የንግድ ስራ አድራሻው ስኮትላንድ ውሰጥ የሆነ ማንኛውም ወገን ራሱን ለእንግሊዝ አገር ፍርድ ቤቶች ወሰን ስልጣን እንዳስገዛ ይታሰባል ወይም በሰሜን አየርላንድ ውስጥ ከሆነ፣ የእንግሊዝ ሃገር ፍርድ ቤቶችን ወሰን ስልጣን ወይም ውሳኔ ለመቀበል እንደተስማማ ይቆጠራል። አንድ ወገን በ ግሬን ኤንድ ፊድ ትሬድ አሶሴሽን ጽሕፈተ ቤት በመተው፣ የፍርድ ሒደቱን ኮፒ ከእንግሊዝ  ውጭ ወዳለ አድራሻ ከተላከለት በትክክል መድረሱ የሚረጋገጥ ሲሆን ተቃራኒ አሰራር ቢኖርም እንኳን ህጉ የበላይነት አለው፡፡

## 25. አለመግባባት እና ግልግል

(ሀ) ሁለቱም ወገኖች ማንኛውንም አለመግባባት በ Gafta የማስማማት ደንቦች 128 መሰረት በቅድሚያ ለመፍታት መሞከር አለባቸው፡፡

(ለ) አንደኛው ወገን መስማማት ለመሳተፍ ካልፈለገ፣ ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ማናቸውም አለመግባባቶች ወይም ከዚህ ውል አተረጓጎም ወይም አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጥያቄዎች በሙሉ በ **GAFTA ቀላል የአለመግባባት ግልግል ደንቦች** 126 መሰረት ይህ ውል በተፈረመበት ቀን በነበረው እትም መሰረት መፈታት እንዳለበት ከስምምነት ላይ ተደርሷል። እነዚህ ደንቦች የዚህ ውል አካል ተደርገው የሚቆጠሩ ሲሆን ሁለቱም ወገኖች የእነዚህን ደንቦች ትግበራ ሙሉ በሙሉ ማወቃቸውንና በዚህም በግልጽ መስማማታቸው ታውቋል፡፡

(c) የዚህ ውል ተዋዋይ ወገኖችም ሆኑ በእነርሱ ስም የሚንቀሳቀስ ማንኛውም አካል በ **GAFTA ቀላል የአለመግባባት ግልግል ደንቦች** 126 መሰረት በግልግል አካል ታይቶ የሚወሰን ማንኛውንም አለመግባባት በተመለከተ ክስ ወይም ሌላ የክስ ሂደት ለማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህም ውሳኔ በሁለቱም ወገኖች ላይ የመጨረሻና አስገዳጅ ይሆናል። ለGafta ወይም ለፍ/ቤቶች ይግባኝ የመጠየቅ መብት አይኖርም። (የፍ/ቤቶች ሚና የግልግል ውሳኔን በማስፈጸም የተወሰነ ነው)

*(መ) በዚህ የግልግል አንቀጽ ውስጥ የተካተተ ማንኛውም ነገር ተዋዋይ ወገኖች ያቀረቡትን ክስ ወይንም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በተመለከተ ዋስትና እንዲሰጣቸው  ከየትኛውም ሀገር ስልጣን ካለው የፍትሕ አካል ከማግኘት የሚያግዳቸው አይሆንም፤ ይሁን እንጂ፣ እነዚህ የፍርድ ሒደቶች ወሰናቸው ለክስ ለተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ዋስትና ለማግኘት ሆኖ የማንኛውም አለመግባባት ፍሬ ነገሮች በ GAFTA ቀላል የአለመግባባት ግልግል ደንቦች 126 መሰረት በግልግል ዳኝነት ብቻ ሊጠየቅ እንደሚገባ ከግንዛቤና ስምምነት ላይ ተደርሷል።*

*(ሠ)* **የግልግል ሒደት ላይ የሚፈጸመ ጥሰት**

ማንኛውም የ Gafta ግልግል ሒደት አካል የሆነ ማንኛውም ወገን (ሀ) የግልግል ውሳኔ በ Gafta በተሰጠ በ21 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ያልፈፀመ ካለ ወይም ለመፈጸመ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም (ለ) በ Gafta ጥያቄ በቀረበለት በ21 ቀናት ውስጥ የግልግል ወጪ፣ ወይም ክፍያን ሳይከፍል ከቀረ፣ ሁለቱም ወገኖች Gafta እንዲህ ዓይነት የግዴታ አለማከበርን ሁኔታ በጽሑፍ ለ GPC እንደሚያሳውቅ በግልጽ ተስማምተዋል። ከዚያም፣ GPC በራሱ ወሰነ ስልጣን መሰረት ጥፋት የፈጸመው ወገን ላይ በ GPC የስነ ምግባር ደንብ እና/ወይም በ GPC ውስጠ ደንቦች/የመተዳደሪያ ደንብ መሰረትና በዚህ ብቻ ሳይወሰን የዲስፕሊን እርምጃ የመውሰድ መብት አለው። የዲስፕሊን እርምጃው ከሚያካትታቸው መካከል ከ GPC አባልነት ማገድ ወይም ከ GPC ተባባሪዎች እንዲታገድ የእገዳ ምክረ ሃሳብ መስጠት ሲሆን ሁኔታዎቹና የእገዳ የቆይታ ጊዜውም በ GPC የሚወሰነ ነው (ማንኛውም የ GPC ኮንቬንሽን ወይም ዝግጅት ላይ መሳተፍን መከልከልና እገዳውን ለ GPC አባልነት ማሳወቅ ይገኘበታል)

## 26. ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽኖች

የሚከተሉት ሕጎች በዚህ ውል ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡

(ሀ) ሽያጭን የሚመለከት ወጥነት ያለው ሕግ ወይም ዩኒፎርም የሽያጭ ህግ እና ዩኒፎርም የው ምስረታና በ1967 የወጣው አለም አቀፉ የሽያጭ ደንብ ፤

(ለ) የተመድ ዓለም አቀፍ የዕቃዎች ሽያጭ ውሎች ኮንቬንሽን 1980።

(ሐ) የተመድ ዓለም አቀፍ የዕቃዎች ሽያጭ ገደብ ላይ የተፈረመ ኮንቬንሽን 1974 እና የ1980 የማሻሻያ ፕሮቶኮል።

(d) ኢንኮተርምስ።

(e) ውሉ በተቃራኒው የሚያትት ማንኛውም መግለጫ ካላካተተ በስተቀር፣ የዚህ ውል አካል ያልሆነ ሰው የውሉን ማንኛውንም ክፍል የማስፈጸም መብት እንደሌለው በ1999 የውል ደንብ (የሶስተኛ ወገኖች መብቶች) ላይ የተደነገገ ነው።

ሻጮች................................................................................................................................ገዢዎች ........................................................................................................................

**የሰጠው አካል፡**

**Global Pulse Confederation**

+ 971.4.363.36.12 | info@globalpulses.org | www.globalpulses.org

Silver Tower, DMCC offices No 1 , Lower Level, JLT, Dubai, UAE, Po Box 340503